የ MCPS ቅጽ 496-1
ማርች 2020
ከ2 ገጽ 1ኛው

# ስለ "Summer RISE 2020" የወላጅ/የሞግዚት የፈቃድ ስምምነት

Summer RISE
Connecting Students to Careers

Partnerships Unit
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
45 West Gude Drive, Room 2301, Rockville, Maryland 20850
የአጋርነት ክፍል/ዩኒት
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

## ወላጅ/ሞግዚት/ብቃት ያለው-ያላት ተማሪ ስምምነት

የሠመር ራይዝ ፐሮግራም የተነደፈው በአሁኑ ወቅት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በመከታተል ላይ ለሚገኙ 11ኛ ክፍል ለሚገቡ እና ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በሠመር ወቅት የሥራ ሙያ ልምዶችን ለመቃኘት የሚያስችል ነው።

1. ግንዛቤ በመውሰድ ስምምነት ተደርጓል በ 2020–2021 የትምህርት ዓመት በ MCPS 11ኛ ክፍል ወይም 12ኛ ክፍል የሚገባ/የምትገባ ተማሪ በሠመር ራይዝ ፐሮግራም/Summer RISE program ሙሉ ተሳትፎ እንደሚያደርግ-እንደምታደርግ እና ሙሉ ሃላፊነት እንደሚወስዱ አውቀውና ተገንዝበው ተስማምተው አጽድቀዋል።

2. ግልጽ መሆኑን በመገንዘብ ስምምነት ተደርጓል ተማሪው(ዋ) በሣምንት 15 - 20 ሠዓቶችን ያሳልፋል/ታሳልፋለች፣ በቀን ከ8 ሠዓት በላይ አይሆንም፣ በሣምንት ከ30 ሠዓት በላይ አይሆንም፣ እና በአጠቃላይ 80 ሠዓት፣ ከ 3 - 4 ሣምንቶች በላይ፣ ሙያዊ ልምድ ትምህርት በሚሰጥ ድርጅት ላይ በእጅ እየተሠራ በመማር እድል መሣተፍ ("Career Experience")። የ "Career Experience" በሣምንት አምስት ቀኖችን፣ ለአራት ሣምንት፣ ከጁላይ 6/2020 ጀምሮ እስከ ጁላይ 31/2020 መጨረሻ ይሠራል። Summer RISE ተሣታፊዎች ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ 8:00 AM በፊት አይጀምሩም ወይም ከ6:00 PM በፊት ያጠናቅቃሉ። ተቀባዮቹ ከ 60 - 80 የሥራ ልምምድ ሠዓቶችን በሠመር ራይዝ ፐሮግራም/Summer RISE Program መጨረሻ ላይ ሊያጸድቁ ይችላሉ።

3. በመገንዘብ ተስማምቻለሁ በ Summer RISE ፕሮግራም ለመሣተፍ፣ ተማሪዎች ስለ ሙያ ክህሎት እና ፋይናንስ አውደጥናት/professional skills and financial literacy workshop በአካል ተገኝተው መሣተፍ እንደሚጠበቅባቸው።

4. በመገንዘብ ስምምነት ተደርጓል የ Summer RISE ፕሮግራም ተሳታፊዎች ከመኖሪያቸው እስከ ሙያ ልምድ የሚማሩበት ስፍራ ድረስ/Career Experience Host location ስለ ራሳቸው መጓጓዣ ሃላፊነት አለባቸው፣ Youth Cruiser SmarTrip® Cards ካርዶች በሁሉም የ MCPS ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ።

5. በመገንዘብ ስምምነት ተደርጓል በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የ Summer RISE ፕሮግራም ሠራተኞች ለተመዘገቡት ተማሪዎች በሙሉ ሙያዊ ትምህርት ልምምድ/Career Experience ለመስጠት የተቻላቸውን ጥረት ሁሉ ያደርጋሉ፣ የሆነ ሆኖ፣ Career Experiences የቦታ መገኘትን መሠረት በማድረግ የሚወሰን ይሆናል። የ Summer RISE ፕሮግራም ሠራተኞች በጂኦግራፊያዊ አካባቢ እና እንደ ኢንዱስትሪው መገኘት ላይ ተሞርኩዘው ተሳታፊ ተማሪዎችን ለመመደብ ይሞክራሉ።

6. በመገንዘብ ስምምነት ተደርጓል የሠመር ራይዝ ፕሮግራም-Summer RISE Program ስንክልና ያላቸው ግለሰቦች የትምህርት ደምብ/Individuals with Disabilities Education Act (IDEA) እና በተጓዳኝ የሜሪላንድ ህግ መስፈርት መሠረት በሚፈለጉት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ዉስጥ አልተካተተም።

7. በመገንዘብ ተስማምቻለሁ የ Summer RISE Program ተሳታፊዎች ምንም እንኳ የሙያ ልምምድ ሠዓቶች የሚሠሩት ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ 8:00 AM እስከ 6:00 PM ቢሆንም የራሳቸውን መርሃ ግብር በቀጥታ የሙያ ልምድ ከሚሰጣቸው ክፍል ጋር ማቀነባበር የራሳቸው ሃላፊነት ይሆናል

8. በመገንዘብ ስምምነት ተደርጓል የ Summer RISE Program ተሣታፊዎች ጥሩ የሆነ የመከታተል ባህርይ፣ መልካም የሆነ ጠባይ፣ ትክክለኛነት፣ በሥነ-ሥርአት መሆን፣ ፈጣን፣ ብስለት፣ ተገቢነት ያለው አለባበስ እና አግባብ የሆነ የሥራ ስነ-ምግባር ያሳያሉ። የ Summer RISE Program ተሳታፊዎች የሙያ ልምድ በሚሰጧቸው ክፍሎች አማካይነት የማይቃለል አይነት ማናቸውም ዓይነት ጉዳይ ወይም ስጋት ካጋጠማቸው የ Summer RISE ፕሮግራም ጽ/ቤትን በ summer-rise@mcpsmd.org ወይም የስልክ ቁጥር፡- 240-740-5599 በመደወል መገናኘት አለባቸው።

9. በመገንዘብ ተስማምቻለሁ የሙያ ልምድ የሚሰጡ ክፍሎች ተጨማሪ የማጣርያ መስፈርቶች ለኖራቸው እንደሚችል። ከጁላይ 6 Summer RISE ፕሮግራም መጀመሪያ ቀን በፊት ማናቸውንም ተጨማሪ የምልመላ መስፈርቶችን ለማሟላት ከሙያ ልምድ አሰልጣኞቻቸው ጋር መሥራት የ Summer RISE Program ተሣታፊዎች ሃላፊነት ነው።

10. በመገንዘብ ተስማምቻለሁ የ Summer RISE Program ተሣታፊዎች አበላቸውን ለማግኘት በየሣምንቱ ግብረመልስ እና ስለ Summer RISE Program ያገኙትን ልምድ በፕሮግራሙ መጨረሻ ላይ የሚሞላ የዳሰሳ ቅጽ ይሞላሉ።

11. በመገንዘብ ተስማምቻለሁ የሙያ ዝንባሌ እና ችሎታ የመሣሠል አንዳንድ የተማሪ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ከማዛመድ/ከማስተያየት ሂደት በኋላ ለሙያ ልምድ ሰጪ ክፍሎች ይሰጣል። የሙያ ሥራ ልምድ ሰጪዎች ስለ Summer RISE Program ተሣታፊዎች የሚያገኙት መረጃ/ኢንፎርሜሽን ከእነርሱ ጋር የተመሣሠለውን ብቻ ነው። ከ Summer RISE Program ተሣታፊዎች የተሰበሰበው መረጃ በጠቅላላ Career Experience Hosts አማካይነት ለማናቸውም ለሌላ ሦስተኛ ወገን እንደማይሰጥ በመገንዘብ ተስማምቻለሁ።

12. በመገንዘብ ተስማምቻለሁ የ Summer RISE Program ተሣታፊዎች ፕሮግራሙን በስኬታማነት ሲያጠናቅቁ በኤሌክትሮኒክስ ቀጥታ የሚተላለፍ ለፕሮግራም ወጪአቸውን ለመሸፈን የታሰበ $300 አበል ያገኛሉ፣ እና የ Summer RISE Program ሲጠናቀቅ MCPS ለ Educational Systems Federal Credit Union የተማሪው(ዋ)ን ስም እና የአያት ስም ይሰጣል። ከባንክ ተቋም ጋር ቀደም ሲል አካውንት የሌላቸው የ Summer RISE Program ተሣታፊዎች ከ Educational Systems Federal Credit Union ጋር ወይም በመረጡበት ባንክ አካውንት የመክፈት ዕድል ይኖራቸዋል። ተሳታፊ ተማሪዎች አበላቸውን ለማግኘት ሙያዊ ክህሎት እና የፋይናንስ አውደጥናት በአካል ተገኝተው በሚሳተፉበት ወቅት የቀጥታ ማስተላለፊያ ቅጽ እንዲያቀርቡ ይጠበቅባቸዋል። የባንክ አካውንት ለመክፈት የተለየ ችግር ካጋጠመ Summer RISE Program ተሳታፊዎች ወይም የእነርሱ ወላጆች/ሞግዚቶች በእነርሱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም በ Summer RISE Program ጽ/ቤት የኮሌጅ እና ሙያዊ መረጃ/ኢንፎርሜሽን አስተባባሪን summer-rise@mcpsmd.org ወይም የስልክ ቁጥር፡- 240-740-5599 በመደወል እንዲገናኙ ይደረጋል።

13. **በመረዳት ተስማምቻለሁ** Summer RISE Program ተሳታፊዎች የ Summer RISE Program በሚጠናቀቅበት ጊዜ በሙያዊ ልምድ ሰጪዎች ዘንድ ሥራ ለመቀጠር የይገባኛል ሁኔታ ስለማይኖር እንደሠራተኛ ለመቀጠር መጠበቅ/ተስፋ ማድረግ አይኖርባቸውም።

14. **በመገንዘብ ተስማምቻለሁ** የሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program ተሣታፊዎች የሰመር ራይዝ ፕሮግራም ሙያዊ ትምህርት ልምድ በሚወስዱበት ጊዜ የአሰሪዎቻቸው/Career Experience Hosts ተቀጣሪዎች ሊሆኑ አይችሉም። የሙያዊ ልምድ ሰጪዎች ከ Summer RISE Program ተሳታፊዎች የሥራ እንቅስቃሴዎች ወዲያውኑ ምንም አይነት የራሳቸውን ጥቅም/advantage አይወስዱም፣አንዳንድ ጊዜ፣ ሥራቸው በእርግጥ ሊደናቀፍ ይችላል። የ Summer RISE Program ተሳታፊዎች በ Career Experience Hosts ሥራ ላይ በቀጥታ እንደማይሳተፉ ወይም በመደበኛነት እንደማይሠሩ፣ ወይም የዘወትር ሥራ (ለምሳሌ�:- ፋይል ማድረግ፣ ሌላ የጽህፈት ሥራቸውን መሥራት፣ ወይም ደንበኞቻቸውን ማስተናገድ) ላይ ጣልቃ እንደማይገቡ ግንዛቤ በማግኘት ተስማምተዋል። የሙያ ሥራ ልምድ ሰጪዎች ለተማሪዎች ስለ ቢዝነስ/ድርጅት እና በሥራ ድርሻ/ሚናዎች ላይ ያተኮረ፣ ኃላፊነቶች፣ እና ስለ ቢዝነሱ/የድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴዎች በሚመለከት ለተማሪዎች ሁሉአቀፍ ግንዛቤ ይሰጧቸዋል። ተማሪው(ዋ)/ተማሪዎቹ እነዚህን ሥራዎች በመሥራት ጥራት፣ ሙያ፣ እና ሥራ አስኪያጅን ወይም ማናጀር ውጤታማ ሆኖ የሚሠራበትን እና በበርካታ የሥራ ቅጥር አካባቢዎች ላይ ለመጠቀም የሚያስችል ጠለቅ ያለ መረዳት/እውቀት ይሻሉ።

15. **በመረዳት ተስማምቻለሁ** የ Summer RISE Program ተሳታፊ በዚህ ስምምነት የተጠቀሱትን ስምምነቶች፣ በ Career Experience Hosts የተዘጋጁት ደንቦች እና መመሪያዎች፣ ወይም ሌላ ማናቸውም የ Summer RISE Program ህጎች በ MCPS ድንጋጌ መሠረት ለመጠበቅ ካልቻለ(ች)፣ የ Summer RISE Program ተሳታፊ ከፕሮግራሙ መባረር ይችላል/ትችላለች እና $300 አበልም ለማግኘት ብቁ አይሆንም/አትሆንም።

## ተጨማሪ ስምምነት

ተማሪ ኦንላይን ሲመዘገብ-ስትመዘገብ፣ ወላጅ/ሞግዚት የሚከተሉትን የተስማሙ መሆናቸውን ተማሪው(ዋ) እያረጋገጠ(ች) ነው:-

- የሠመር ራይዝ ተማሪ ቪድኦ እንዲቀረጽ-እንድትቀረጽ፣ ፎተግራፍ እንዲነሣ-እንድትነሣ፣ እና/ወይም በሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program የሆነ ጊዜ ላይ ሪኮርድ እንደሚደረግ-እንደምትደረግ መፈቀዱን ያመለክታል። እነዚህ ምስሎች እና/ወይም ሪኮርድ የተደረጉ ነገሮች ስለ Summer RISE ማስተዋወቅን ጨምሮ ምስሎቹን ለመጠቀም ማሳወቅ አስፈላጊ ሳይሆን ለተለያየ ዓላማ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። በዚህ መልክ ጥቅም ላይ ስለማዋላቸው ተማሪው(ዋ) ምንም ካሣ አይከፈለውም/አይከፈላትም እና MCPS ሁሉንም ምስሎች፣ ቪድዮዎች፣ እና የተቀረጹ/የተቀዱ ነገሮችን እና ከእነርሱ የተቀዱ ወይም የተወሰዱ ሥራዎችን የመጠቀም መብት አለው።
- የሠመር ራይዝ/Summer RISE ተማሪ "Career Experience Host or Summer RISE" ሠራተኛ አማካይነት ከሥራ ጋር ለተገናኙ ሁነቶች የሚነዳ የግል ወይም የሥራ ተሽከርካሪ ላይ ተሳፋሪ ለመሆን ተፈቅዶለ(ላ)ታል፣ ነገር ግን ተማሪው(ዋ) እና ወላጅ/ሞግዚት MCPS ን እና ሙያዊ ልምድ ትምህርት የሚሰጠውን/Career Experience Host ማናቸውም አይነት ጉዳት ቢደርስ ተጠያቂ እንደማያደርጉ ግንዛቤ በማድረግ ስምምነት ተደርጓል።
- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሠመር ራይዝ ፕሮግራም ሠራተኞች/MCPS Summer RISE program staff ወይም የሙያ ሥራ ልምምድ ተቀባይ/Career Experience Host ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም የምዝገባ ቅጽ ላይ የሰጡትን ስልክ በመጠቀም ለተማሪው(ዋ) ይደውላሉ ወይም ቴክስት ይልካሉ።

## ፊርማ

በሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program ለመሣተፍ የወላጅ/የሞግዚት ስምምነት መኖሩን ለማረጋገጥ የ "Summer RISE" ተማሪ የኤሌክትሮኒክ ፊርማ ይፈርማል/ትፈርማለች። በምዝገባ ወቅት፣ ጁላይ 2020 በድንገተኛ/አስቸኳይ ጊዜ ለማግኘት የሚቻል የወላጅ/የሞግዚት ስም፣ የስልክ ቁጥር፣ እና የኢ-ሜይል አድራሻ ያስፈልጋል።